ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON M6H - 1L8
**Tel./ Fax: 416 - 516 1244**

# መሪዎችንና ሕዝብን መለያየት አይቻልም

በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ፕሬዚዳንት የሚመራው የልዑካን ቡድን በአሜሪካ የሚያደርገውን የሥራ ጉብኝት በመቀጠል በቶሮንቶ ካናዳ ለፌብርዋሪ 24 ቀን 2008 ዓ.ም ፕሮግራም አስቀድሞ የተያዘ መሆኑን ይታወሳል።

በዚያም መሰረት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ፌብርዋሪ 17 ቀን እጅግ ደማቅና የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ ከተከናወነ በኋላ የድል ጽዋውን ወደ ቶሮንቶ ካናዳ ለማምጣት የልዑካን ቡድኑ ሲዘጋጅ፤ የካናዳ ቪዛ ስለሚያስፈልጋቸው ማመልከት ነበረባቸው። በዚያም መሰረት ፌብርዋሪ 19 ቀን በዋሽንግተን ዲሲ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ከባለቤታቸው ጋር እንዲሁም ወይዘሮ ንግሥት ገብረሕይወትም በዚሁ እለት አስፈላጊውን የቪዛ ማመልከቻ አሟልተውና ክፍያ አጠናቀው ሲያበቁ፤ የካናዳ ኤምባሲ ቪዛ ለማግኘት የግዴታ አስር ቀናት መጠበቅ አለባችሁ ስላለ የፌብርዋሪ 24ቱን የቶሮንቶ ስብሰባ ወደ ማርች 9 ቀን እንዲተላለፍ ተደረገ።  የተባሉት አስር ቀናት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደካናዳ ኤምባሲ ሄደው ቢጠይቁ "የእናንተ ቪዛ ከኦታዋ ስለሚመጣ ጠብቁ ይሰጣችኋል" ስለተባሉ በየጊዜው እየሄዱና ስልክ እየደወሉ ቢጠይቁም "ገና አልመጣም" ጠብቁ እያሉ ሳይሰጣቸው ማርች 9 ቀን እየቀረበ መጣ።

ሌላው የልዑካኑ ቡድን አባል ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት በፌብርዋሪ 26 ቀን ዋሽንግተን ዲሲ የካናዳ ቪዛ ሲያመለክቱ አስፈላጊውን ማመልከቻ ሞልተውና ከሚያስተምሩበት ዩንቨርሰቲ የሥራ ደብዳቤ ተጽፎላቸው ለቪዛ ማመልከቻ የሚደረገውን ክፍያ ከፍለው ሲያመለክቱ አስር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ "አንተ ካናዳ ሄደ ትቀራለህ ስለዚህ ቪዛ አንሰጥህም" በማለት ካናዳ ሶስቴ ገብተው የወጡና በአሜሪካ አገር ዩንቨርስቲ ፕሮፌሰር ሆነው እየሰሩ ያሉትን ሰው ማመልከቻውን እንኳን ሳይመለከቱ ከለከሏቸው።

በእነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቪዛ መዘግየትና የዶክተር ታዬ ያለምንም ምክንያት መከልከል ትክክል ባለመሆኑ ማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ለመሞከር በተደረገው ጥረት፤ ዋሽንግተን ዲሲ በካናዳ መንግሥት ሥራ ላይ በሚኖሩ ካናዳዊ አማካኝነት እና ተጠይቆ ይሰጣቸዋል ይጠብቁ የሚል መልስ እየተሰጣቸው ቆየ። ከዚያ በተጨማሪ በቶሮንቶው የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት የቦርድ አባል አማካኝነት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የካናዳ መንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣን ችግሩን አስረድተው የቪዛው ሁኔታ እንዲፋጠንላቸው እና የተከለከሉት እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ባለሥልጣኑ በእርግጠኛነት "ሰዎቹ ይመጣሉ ሁሉንም መረጃ በልዩ ረዳቴ በኩል ላኩልኝ" ስላሉና ለልዩ ረዳታቸውም ትእዛዝ ስለሰጡ፤ በዚያው መሰረት አስፈላጊውን መረጃ በመዘርዘር፤ ማለትም ማርች 9 ቀን 2008 ዓ.ም ለአንድ ቀን በሚደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ እንዲገኙና ኢትዮጵያውያንን እንዲያመሰግኑ የጥሪ ደብዳቤ እና ቪዛ እንዲሰጣቸው ለካናዳ ኤምባሲ የተጻፈ ደብዳቤ፣ የፌብርዋሪ 24 የተሰረዘውንና አዲሱን የማርች ዘጠኙን የደርሶ መልስ የአየር ቲኬት፣ የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያዎችን ጨምሮ በመላክ መልሱን ይጠባበቅ ጀመር። የሚኒስትሩም ልዩ ረዳት የተመደበው ሰው ጉዳዩን እንደሚያስጨርስ ተስፋ ሰጥተውን እየተከታተልን እያለ በስልክ ባደረጉት ግንኙነት ጉዳዩን እየሰሩበት መሆኑን ሌላው የተመደበው ሰው አስታውቆ ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት እና ወይዘሮ ንግሥት ገብረሕይወት ወርቁ ግን ለቪዛ ማመልከቻ አላስገቡም አስገብተዋል ካላችሁ ቀኑንና ቦታውን ንገሩን በማለት ኦታዋ የምንደውልበትን ቁጥር ይሰጣሉ። በዚያም መሰረት ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት ያመለከቱበትን ቀንና ቦታ እንዲሁም ቪዛ የተከለከሉበትን ደብዳቤ ቁጥርና

ወይዘሮ ንግሥት ለቪዛ ያመለከቱበትን ቦታና ቀን መረጃ ሰጠን። የለም ወይዘሮ ንግሥት ከዋሽንግተን ዲሲ አላመለከቱም የሚል መረጃ ከኦታዋ ሲነገረን፤ ለማመልከቻ የከፈሉበት ደረሰኝ በወይዘሮ ንግሥት እጅ እያለ አላመለከቱም ሲባል የሚያስገርም ነገር ነው።

ለኢንጂነር ኃይሉ ሻውልና ለባለቤታቸው ቪዛ ይሰጣቸዋል ተብሎ እስከ አርብ ከሰዓት በኋላ ድረስ ቢጠብቁም ከኤምባሲው መልስ ባለማግኘታቸውና ወደ ካናዳ የሚመጡበት የበረራ ሰዓታቸው በመድረሱ ጉዞው እንዳልተሳካ በመገንዘብ ሌላ የመገናኛ አማራጭ እንዲፈለግ ተደርጓል።

ከዚህም በተጨማሪ አቶ ማሙእሸት አማረ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባል ከአዲስ አበባ ወደ ካናዳ እንዲመጡ ከተወከሉት ልዑካን መካከል አንዱ በመሆናቸው በኦገስት 2007 አመልክተው ሳይሰጧቸው ቀርተው በድጋሚ ጽህፈት ቤታችን የጥሪ ደብዳቤ ልኮላቸው እንደገና በዲሴምበር 2007 ዓ.ም ለካናዳ ኤምባሲ አመልክተው ይኸው ከሶስት ወር በላይ የካናዳ ኤምባሲ ፓስፖርታቸውን ይዞ ቪዛ አልሰጣቸውም ወይም ቪዛ ከልክሎ ፓስፖርታቸውን አልመለሰም። የአንድን ሰው ፓስፖርት ለዚህን ያህል ወራት መያዙ የዚያን ግለሰብ የመንቀሳቀስ መብት መከልከል አይደለምን? ይህ ሁሉ ምንን ያሳያል? ለምንና በምን ምክንያት ቪዛ እንዳይሰጣቸውና ይህ ሁሉ የማዘግየትና የመከልከል ሥራ ተፈጸመ? በምንስ ምክንያት ነው ለአቶ ደበበ እሸቱ እና ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ለእነ ልደቱ አያሌው እና ዶክተር በየነ ጴጥሮስ ቪዛ ሲሰጥ ለእነ ኢንጂነር ኃይሉ፣ ወይዘሮ ንግሥት፣ አቶ ማሙእሸትና ዶክተር ታዬ፣ የተከለከለው? ከዚህ በፊትም የአሜሪካ ኤምባሲ ለሌሎች የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላት ቪዛ ወዲያውኑ ሲሰጥ አስቸኳይ ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ለክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ግን ወደ ሁለት ወር ገደማ አዘግይቶ ሲያበቃ ወደ ጀርመን ሊሄዱ ሲነሱ ነበር የአሜሪካ ቪዛ የተሰጣቸው። **ይኸ ሁሉ የተቀነባበረ ሴራ የሕዝብ መሪዎችና ወገን የሆኑትን ከሕዝብ ለማለያየትና ላለው አገዛዝ ታዛዥ የሆኑትን ብቻ በማንቀሳቀስ የወያኔን እድሜ ለመቀጠል የሚደረግ ከንቱ ሙከራ መሆኑን ሁሉም ወገን ሊያጤነው ይገባል።**

የካናዳ መንግሥት የወያኔን አገዛዝ ሲደግፍና የሚፈጸመውን ሰብዓዊ መብት መጣስ የሰው መገደልና መታሰር ከምንም ሳይቆጥር የእርዳታ ገንዘብ ሲለግስ ቆይቷል፣ እየሰጠም ይገኛል። የካናዳ መንግሥት ሕዝቡን ከሚገድል፣ ከሚያስርና ከሚያሰቃይ በሕዝብ ያለተመረጠ መንግሥት ጋር መቆሙን ትቶ ከ 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲቆም በርካታ ደብዳቤዎችን በመጻፍና፣ ሰላማዊ ሰልፎችን በማድረግ በካናዳ ያሉ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። ሰሚ ግን አልተገኘም።

አሁንም ቢሆን እንደ ካናዳዊ ዜግነታችን ማግኘት የሚገባንን መብት ሲጣስብን እና ስንከለከል ዝም ብለን አንመለከትም። የምንፈልጋቸውን ሰዎች የመጋበዝ እና የማየት መብት ሊነፈገን አይቻልም። **የቶሮንቶ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት መሪዎቹ ወደ ካናዳ መጥተው ሕዝቡን እንዳያመሰግኑና ተገናኝተው እንዳይወያዩ በቪዛ ማዘግየትና መከልከል የተደረገውን ሙከራ ጨርሶ የማይቀበለው መሆኑን እና ለምንና በምን ምክንያት ይህ እንደተደረገ የካናዳን መንግሥት ይጠይቃል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህንን ሁኔታ ተገንዝቦ የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግና ትብብሩን እንዲያሳይ ጥሪያችንን እናቀርባለን።**

መሪዎቻችንን ከእኛ መለየት አይቻልም። ምንም እንኳን በአካል ለመምጣት እንዳይችሉ ቢደረግም በቪዲዮ እያዩንና እያዳመጡን እኛም እያየንና እያዳመጥናቸው ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ለመወያየት፣ ጥያቄና መልስም ለመስጠት ተችሏል። ይህን የቪዲዮ ኮንፈረንስ አሜሪካ ባሉ ታታሪ ወገኖቻችንና ቶሮንቶ ባሉ ቆራጦች አማካኝነት ተቀነባብሮ የተከለከልነው የመገናኘት እድል ከሽፎ፤ የአንድነት ኃይሉ አንድ የድል ምዕራፍ አስመዝግቦ ሲያልፍ እንዳይሳካ ያደረጉ ክፍሎች ከትዝብት በቀር ያተረፉት ነገር የለም።

ወደፊት ለሚጠብቀን ትግል በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ፊት የገባነውን ቃል በመጠበቅ ምንም ምድራዊ ኃይል ትግላችንን ሊያከሽፍና ሊያስቆመን እንደማይችል እናረጋግጣለን።

ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት
ጽህፈት ቤት
ቶሮንቶ፤ ካናዳ

ማርች 11 ቀን 2008